# የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርጥበት እጥረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2
## ግንቦት 22/2018 ዓ.ም.


**መግቢያ**

ኢትዮጵያ በተራዘመ እርጥበት እጥረት እና በአለም አየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ለተፈጥሮ አደጋ ክስተቶች መንስኤዎች ተጋላጭ ሆና ቆይታለች፡፡ አሁንም በተለያዩ ኪስ ቦታዎች የመጋለጥ እድሏ ከፍተኛ ነው፡፡ ታሪካዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የአገሪቱ ሰሜናዊና ምስራቃዊ አካባቢዎች ማለትም ትግራይ፣ አፋር፣ ምስራቃዊ አማራ፣ ኦሮሚያ (ምስራቅና የስምጥ ሸለቆ አጎራባች የሆኑ ቦታዎች)፣ በሶማሌ ሰሜናዊ ክፍል፣ ድሬ ዳዋ እንዲሁም ጥቂት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል እና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የዝናብ እጥረት ተጋላጭ እንደነበሩ ያሳያል፡፡ ለዚህም ዋና ምንስኤ የሚሆነው የፓስፊክ ውቅያኖስ መካከለኛውና ምስራቃዊ ክፍል ከመደበኛው በላይ መሞቅ በክረምት ዝናብ መጠንና ስርጭት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ዋነኛው ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት የአገሪቱ አካባቢዎች በአመት ሁለት ጊዜ ዝናብ የሚያገኙ ቢሆንም ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸው ክረምት (ከሰኔ እስከ መስከረም) ወር የሚሸፍን ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ በየሚኖርበት ጊዜ በአብዛኛው ሰብል አብቃይ በመሆናቸው በሰብል ምርት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ እንዲሁም በውሃ አቅርቦት፣ በእንሰሳት የሰውነት ሁኔታና በእንስሳት ተዋፅኦ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ተያያዥነት ላላቸው የአዝዕርት በሽታ መከሰት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የምግብ እጥረት ለሚጋለጡ የማህበረሰብ አካላት መጨምር አስተዋፆ ያደርጋል፡፡

**በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት 2026 ክረምት ወቅት የተሰጠ ትንቢያ**

በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ከተሰጠዉ የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ አዝማሚያ ትንበያ እንደሚያመለክተው ዋነኛ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሰሜን ምስራቅና የምስራቅ የአገሪቱ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በታች ያመዘነ እንዲሁም በመካከለኛውና በሰሜን ምዕራብ መደበኛና ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚኖር ተመላክቷል፡፡

- በመሆኑም የክረምት 2018 ወቅቱ ዝናብ አገባቡ በደቡብምዕራብ ከመደበኛው ቀደም ብሎ እንደሚገባና በተቀረው የአገሪቱ ክፍል በመደበኛ ሁኔታ እንደሚገባ ፡፡
- በክረምቱ መግብያ በሰኔ ወር እና መውጫ በመስከረም ወር የዝናቡ ስርጭት የተዛባና ደረቅ ሰሞናት የሚዘወተርበት እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡
- አልፎ አልፎ የሚኖር የከባድ ዝናብ ክስተት ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በመካከለኛው፣ በምስራቅና በሰሜንምስራቅ የክረምቱ ዝናብ ቀደም ብሎ እንደሚወጣ፡፡
- በደቡብ ትግራይ፣ በአፋር፣ በምስራቅ አማራ እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛ እና ከመደበኛ በታች ያደላ የዝናብ መጠን እንደሚጠበቅ፡፡
- ምዕራብ ትግራይ እና አማራ መደበኛ እና ከመደበኛ በታች ዝናብ እንደሚያገኙ፡፡ የቤኒሻጉልጉሙዝ፣ የምዕራብ ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ እና ደቡብምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚሆን፡፡
- የሰሜን ሶማሌ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን፣ የደቡብ እና የምስራቅ ኦሮሚያ እና የመካከለኛው ኢትዮጵያ ክልሎች በአመዛኙ መደበኛ ዝናብ እንደሚያገኙ ትንበያ ተሰጥቷል፡፡




**Tercile probability for Kiremt 2026**

**Source: - EMI**

**ለ2018 የክረምት ወቅት የተመረጡ ተመሳሳይ አመቶች 1997 እና 2023 እ.አ.አ ናቸው**

# የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርጥበት እጥረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2
# ግንቦት 22/2018 ዓ.ም.

## የዚህ ማስጠንቀቂያ ዓላማዎች

- ሕብረተሰቡ በአካባቢው የሚጠበቀውን የእርጥበት እጥረት አስቀድሞ እንዲገነዘብ ማድረግ፡፡
- በዚህ መሠረት በሰብል ልማት፣ በእንስሳት፣ በውኃ አቅርቦት፣ በጤና፣ በምግብ ዋስትና እና ሌሎችም ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ ለመከላከል ቅድመ እርምጃ እንዲወሰድ ማነሳሳት፡፡
- የመንግሥት አካላት፣ ፈፃሚ ተባባሪ አካላት፣ የግል ድርጅቶች እና ህብረተሰቡ አስፈላጊውን የመከላከልና አደጋውን የመቀነስ እርምጃዎችን እንዲወስድ ለማንቃት ነው፡፡

## የማስጠንቀቂያው ጊዜ ወሰን እና መሠረት

- ይህ የድርቅ ቅድመ የማስጠንቀቂያ መልዕክት የተዘጋጀው በቅርቡ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስትቲዩት ለተጠቃሚዎች ባዘጋጀው እና በተሰራጨው የክረምት የአየር ጠባይ ትንበያ መሰረት ሲሆን የሚሸፍነው ከሰኔ 2018 እስከ መስከረም 2019 እ.ኢ.አ ያለውን ጊዜ ይሆናል፡፡ በየወቅቱ በሚኖረው የአየር ፀበይ መቀያየር ምክንያት ነባራዊ ሁኔታውን ሊቀየር ስለሚችል በሚደረገው ተከታታይነት ያለው ትንተና የቅድመ ማስጠንቀቂያው ይዘት ሊቀየር ይችላል፡፡

## 2018 ዓ.ም ክረምት ዝናብ ተጋላጭ አካባቢዎች

በዚህ መሠረት በዘንድሮ የክረምት 2018 ዓ.ም ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑ አካባቢዎች ማለትም በአማራ ክልል ዋግኽምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ፣ ምስራቅ ጎጃም ምስራቃዊ ወረዳዎች፣ ደቡብ ጎንደር እና ማከላዊ ጎንደር ዞኖች፣ ኦሮሞ ዞን እና የሰሜን ሸዋ ዞን ቀላማ ወረዳዎች፣ አፋር በሁሉም ዞን፣ በትግራይ ክልል የምስራቃዊ፣ ደቡባዊና ደቡብ ምስራቅ ዞኖች፣ ሶማሌ ክልል ፋፈን እና ሲቲ ዞኖች፣ ድሬ ዳዋ፣ በኦሮሚያ ክልል ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ አጎራባች ወረዳዎች እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ አጎራባች ወረዳዎች ላይ የሚጠበቀዉ ዝናብ መደበኛና ከመደበኛ በታች የመሆን እድል እንዳለ በኢትዮጵያ ሜትሪዮሎጂ ኢንስቲትዩት ተተንብይዋል፡፡

ይህ የድርቅ ወይም የእርጥበት እጥረት ስጋት ቅድመ ማስጠንቀቂያ ቁጥር 2 ግንቦት 22/2018 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት እ.ኤ.አ በ2026 ለክረምት ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ እዝማሚያን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ሲሆን በ2018 ዓ.ም በዝናብ ማነስ ጉዳት ሊደርስባቸዉ የሚችሉ አካባቢዎችን በመለየት ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** በተጠቀሱት ወረዳዎች በሁሉም የወረዳው አካባቢዎች ላይ የዝናብ እጥረት ይከሰታል ማለት እንዳልሆነ እንዲታወቅና እንደየአግሮኢኮሎጂ ዝናብ እጥረቱ ከቦታ ቦታ በመጠንም ይሁን በሽፋን ሊለያይ እንደሚችል ይታወቅ፡፡


# የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርጥበት እጥረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2

## ግንቦት 22/2018 ዓ.ም.

### የ2018 በክረምት ወቅት ለዝናብ እጥረት ተጋላጭ ወረዳዎች

| ክልል | ዞኖች | ወረዳዎች |
|---|---|---|
| ትግራይ | ሰሜን ምዕራብ | ታህታይ አድያቦ, አስገዴ, ጸለምቲ አድያቦ, ፂምበላ |
| | ማዕከላዊ | ጨኢላ, አእፈሮም, አድዋ, ላዕላይ ማይጨው, ታህታይ ማይጨው, አድዋ, ቆላ ተንበይን, አበርገሌ |
| | ምስራቃዊ | ጉሎመክዳ, ጋንታአፋሾም, ሃውዜን, አፅቢ, ፀዳአምባ |
| | ደቡባዊ | እባላጄ, ኦፍላ, ጨርጨር |
| | ደቡብምስራቅ | እንደርታ, ህንጣሎ, ሳመረ, ዋጅራት |
| አፋር | አውሲ/ዞን 1 | ኤሊዳር, አሳይታ, አፋምቦ, ሚሌ, ጭፍራ, ዱብቲ, ቆሪ, አዳር |
| | ክልባቲ/ዞን 2 | ኤርበቲ, ኩነባ, ዋሳማ, መጋሌ, በረሃሌ, ዳሎል, አፍዴራ, ቢዱ, አባላ |
| | ጋቢ/ዞን 3 | አሚባራ, አዋሽ ፈንታሌ, ዱለቻ, ገዋኔ, ገላሉ, አቢዳ, ቡሬሙዳይቱ, አርጎባ, ሀሩንቃ |
| | ማሂ/ዞን 6 | ያንጉዴ, ኪላሉ |
| | ፋንቲ/ዞን 4 | አውራ, እዋ, ቴሩ, ማባይ, ያሎ, ጉሊና |
| | ሃሪ/ዞን 5 | ተላላክ, ሰሙሮቢ, ዳዌ, ዳሊፋጊ, ሃድሊላ |
| አማራ | ሰሜን ጎንደር | አደርቃይ, በየዳ, ጃናሞራ, ዳባት |
| | ደቡብ ጎንደር | እምናት, ፋርጣ, መና መከተዋ |
| | ሰሜን ወሎ | ቡገና, ራያ ቆቦ, ጊዳን, መቄት, ዋድላ, ጉባላፍቶ, ሀብሩ, ላስታ, ዳዉንት |
| | ደቡብ ወሎ | ተንታ, ኩታበር, ተለሁደሬ, ደላንታ, ቃሉ, አልቤኮ, ደሴ ዙሪያ, ለጋምቦ, ወርኢሉ, መቅደላ |
| | ሰሜን ሸዋ | ሚዳአሮሞ, መረሃቤቴ, መንዝጌራምድር, በረኸት |
| | ዋግኽምራ | ዝቋላ, አበርገሌ, ሰቆጣ, ደሃና, ጋዝ ጊበላ, ሳህላ |
| | አርጎባ ልዩ | አርጎባ |
| | ኦሮሞ | ዳዋ ጨፋ, ጅሌ ጥሙጋ, አርቱማ ፉርሲ, ዳዋሃረዋ |
| | ማዕከላዊ ጎንደር | ወገራ, ምዕራብ በለሳ, ኪንፋዝ |
| ኦሮሚያ | ሰሜን ሸዋ | አብቹናኘኣ, ቅንብቢት |
| | ምስራቅሸዋ | ፈንታሌ, አዳሜቱሉ ዲጆከምቦልቻ |
| | አርሲ | አሰኮ |
| | ምዕራብ ሃረርጌ | ዶባ, መሰላ, አንቻር, ጉባቆርቻ, ሃብሮ, ቦኬ, ቁኒ, ጭሮ ዙሪያ, ጉቦርደዴ |
| | ምስራቅ ሃረርጌ | ኮምቦልቻ, ጉርሱም, ባብሌ, ፌዲስ, ቀርሳ, ሜታ, ጎሮጉቱ, ደደር, መልካቦሎ, በደኖ, ግራዋ, ጎሮሚቲ |
| | ምዕራብ አርሲ | ሲራሮ, ሻላ, አርሲ ነገሌ |
| ሶማሌ | ሲቲ | ደንበል, ሽንሌ, ኤረር, አፍደም, ሚኤሶ, ጎታቢኪ |
| | ፋፈን | አውበሬ, ሃርሸን |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ማረቆ ልዩ | ማረቆ ልዩ ወረዳ |
| | ሃድያ | ሻሸጎ, ምስራቅ ባደዋቾ, ምዕራብ ባደዋቾ, ዱና |
| | ሃላባ | ዊራ |
| | ከምባታ | ቀዲዳ ጋምቤላ, ቃጫ ቢራ |
| | ስልጤ | ሲልጢ, ዳሎቻ |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ | ቦሎሶ ሶሬ, ዳሞት ጋሌ, ዳሞት ወይዴ, ሁምቦ, ኪንዶ ኮይሻ, ኦፋ |
| ሲዳማ | (አልተገለጸም) | ሸበዲኖ, ዳሌ |

# የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርጥበት እጥረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2
## ግንቦት 22/2018 ዓ.ም.




የኢትዮጵያ ሜትሪዮሎጂ ኢንስቲትዩት በክረምት ወቅት ሊኖር የሚችል የአየር ፀባይ ትንበያ መሰረት የ2018 ክርምት ወቅት ለዝናብ እጥረት ተጋላጭ ይሆናሉ ተብለው የተለዩ ወረዳዎችን የሚያመለክት ካርታ

**ምንጭ፡ ኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን**

# የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርጥበት እጥረት
## ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2
## ግንቦት 22/2018 ዓ.ም.

**የ2018 ዓ.ም ክረምት ድርቅ ቅድመ ማስጠንቀቂያና ቅድመ እርምጃ ማጠቃለያ ሰንጠረዥ**

| ቦታዎች | የሚጠበቁ ቁልፍ ተግባራት | ባለድርሻ አካላት |
|---|---|---|
| 📢 በሁሉም ቦታዎች የቅድመ ማስጠንቀቂያው መረጃ ለማህበረሰብ በማድረስ እና ግንዛቤ መፍጠር | • ክረምቱን በተመለከተ የማስጠንቀቂያውን በቀጥታ ለማህበረሰብ ማድረስ<br>• በማህበረሰብ አውደ ሰብሳቢዎች፣ በአደባባይ ማስታወቂያ፣ በመስጂድ/ቤተክርስቲያን ድምጽ ማጉያ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ማሰራጨት::<br>• በወረዳ ደረጃ "ቅድመ ዝግጅት ኮሚቴ" በመፍጠር እያንዳንዱ ቀበሌ ምን እርምጃ እንደሚወስድ ማወቅ::<br>• አርሶ አደሮች ልምዳቸውን እንዲለዋወጡ እና አነስተኛ የውሃ አያያዝ ቴክኒክ እንዲማሩ ማድረግ::<br>• የተቀናጀ ዘርፈ-ብዙ የጎርፍ መጠባበቂያና ምላሽ እቅድ ማዘጋጀት | • ሚዲያ (ኤፍኤም ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣<br>• የሃይማኖት ተቋማት<br>• የአካባቢ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች<br>• ኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት፡<br>• የአደጋ ስጋት ኮሚሽኖች |
| 1. 🟠 **ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ቦታዎች:** ሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና በደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች<br>2. 🟡 **ጥንቃቄየ ሚፈልጉ ቦታዎች:** በደቡብ ትግራይ፣ በአፋር፣ በምስራቅ አማራ፣ በምስራቅ ኦሮሚያ እና በሶማሌ አንዳንድ ዞኖች<br>3. 🔵 **ቀጣይነት ክትትል የሚፈልጉ:** በደቡብ እና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ አንዳንድ ወረዳዎች | **ውሃ ማከማቸትና መጠበቅ**<br>• የውሃ ጉድጓዶች እና ኩሬዎች ጥገና በፍጥነት ማከናወን::<br>• ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ውሃ ለመሰብሰብ ጣሪያዎችን፣ ገንዳዎችን እና ጊዜያዊ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ማዘጋጀት::<br>• የመሬት ውስጥ ውሃ ለማቆየት (በተለይ በቆላማ አካባቢዎች) ጉድጓድ መቆፈር ወይም መልሶ ማደስ::<br>• የውሃ ማጠራቀሚያ ቁሳቁስ ማቅረብ | •ክልሎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ቀበሌዎች:<br>•የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር/ቢሮዎች<br>•ማህበረሰቡ፣<br>•አጋር አካላት |
| | **ግብርና እና እንስሳት**<br>• ድርቅን የሚቋቋሙ የአጭር ጊዜ የዘር ዝርያዎችን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ እና መዝራት፤<br>• ገና ዝናብ ሳይጀምር መሬት ማረስ እና ዝናብ በሚዘንብበት ጊዜ ለመዝራት ዝግጁ ማድረግ::<br>• የአፈር እርጥበት ማስጠበቂያ ስልቶችን መተግበር<br>• የመኖ ዋጋ አለመጨመር ላይ ክትትል ማድረግ<br>• የግጦሽ መሬት በማህበረሰብ ደረጃ በማቀድ በቁጠባ መጠቀም::<br>• የእንስሳት መኖ እና ተጨማሪ ግብዓት ቀድመው ማከማቸት:: | •ግብርና እና የእንስሳት ሀብት ልማት ሚኒስቴ/ቢሮዎች፣<br>•የግሉ ዘር ድርጅቶች<br>•ማህበረሰቡ፣<br>•አጋር አካላት |
| | **ጤና እና ማህበራዊ ጥንቃቄ**<br>• ከውሃ እጥረት ጋር ተያይዘው የሚመጡ በሽታዎችን (ተቅማጥ፣ ኮሌራ) ለመከላከል ንጹህ ውሃ አቅርቦት ላይ መሥራት::<br>• እርጉዝ እና አጥቢ እናቶች፣ ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ በቀበሌ ደረጃ መሥራት::<br>• አስፈላጊ መድሃኒቶች በክምችት ማቆየት | •ጤና፣ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር/ቢሮዎች<br>•ማህበረሰብ፣<br>•የግል ድርጅቶች፣ ትምህርት ቤቶች፣ ፋርማሲዎች |

# የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኮሚሽን የእርጥበት እጥረት
# ቅድመ ማስጠንቀቂያ መፅሄት ቁጥር-2
# ግንቦት 22/2018 ዓ.ም.

**ማስታወሻ፡-**

- ይህ የድርቅ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ቁጥር 2 ግንቦት 22/2018 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት እ.ኤ.አ በ2026 ለክረምት ወቅት የአየር ጠባይ ትንበያ እዝማሚያን መሠረት በማድረግ የተሰጠ ሲሆን በቀጣይ ደግሞ ከኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ በየጊዜዉ የሚሰጠዉን የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ትንበያ መከታተል አስፈላጊ ይሆናል፡፡